# የብርሃን ባንክ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ

# እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ

# ጥቅምት 18 ቀን 2018 ዓ.ም.

መግቢያ ..... 4

**ክፍል አንድ ..... 6**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች..... 6**

አንቀጽ 1 ርዕስ ..... 6

አንቀጽ 2. ትርጓሜ..... 6

አንቀጽ 3 ስለጾታዊ አገላለጽ፤ ..... 8

**ክፍል ሁለት ..... 8**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈፃፀም ፖሊሲ ..... 8**

አንቀጽ 4 . የቦርድ አባላት ምርጫ ፖሊሲ መርሆዎች፤..... 8

**የባንኩ የምርጫ ፖሊሲ መርሆዎች የሚከተሉትን ያካትታል። ..... 8**

አንቀጽ 5  የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው ስልጣንና ሃላፊነት ........................................................................................ 9

አንቀጽ 6 የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና ምርጫ ጊዜያዊ ኮሚቴ አባላት ........................................................... 10

አንቀጽ 7 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ብዛትና ስብጥር ..................................................................................... 10

አንቀጽ 8 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ ................................................................................................. 11

አንቀጽ 9 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ማሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች .......................................................... 11

አንቀጽ 10 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ................................................................................................. 12

**ክፍል ሦስት.................................................................................................................................. 13**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ ........................................................... 13**

አንቀጽ  11 የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና ምርጫ ጊዜያዊ ኮሚቴ አባላት አመራረጥ ................................... 13

አንቀጽ 12 የጊዜያዊ ኮሚቴው አባላት የሚመረጡበት መስፈርት............................................................................ 13

አንቀጽ 13 የጊዜያዊ ኮሚቴው ሀላፊነቶች........................................................................................................... 13

አንቀጽ 14 ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች ............................................................ 15

አንቀጽ 15 ገለልተኛ ዳይሬክተሮች ሊያሟሉት የሚገባው መስፈርት ...................................................................... 18

አንቀጽ 16  የምርጫ መስፈርቶችንና ፕሮሲጀር (ሂደት) ለባለአክሲዮኖች ስለማሳወቅ ........................................ 19

አንቀጽ  17  እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ  አባላት የጥቆማ ሂደት ............................................................................. 19

አንቀጽ  18 የድምፅ አሰጣጥ ሂደት..................................................................................................................... 22

**ክፍል አራት.................................................................................................................................. 25**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ...................................................................................................................... 25**

አንቀጽ  19   ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የማይሆንበት ሁኔታ ........................................................................................ 25

አንቀጽ 20 ድጋፍ ስለማግኘት ........................................................................................................................ 25

አንቀጽ 21 የሌሎች ሕጐች ተፈጻሚነት.......................................................................................................... 25

አንቀጽ 22 መሻሪያ ...................................................................................................................................... 26

አንቀጽ 23 ከዚህ ፖሊሲ እና መመሪያ ጋር ስለሚቃረኑ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ........................................... 26

አንቀጽ 24 ማሻሻያ ....................................................................................................................................... 26

አንቀጽ 25 ተፈጻሚነት................................................................................................................................. 26

# መግቢያ

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚሾሙትና የሚመረጡት በአክስዮን ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንደሚሆን በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 296(1) እና 298(2) ተደንግጓል፡፡ ይህንን ሕግ መሰረት አድርጎ የተቋቋመው ብርሃን ባንክ አ.ማ. በመመስረቻ ጽሁፉ አንቀጽ 17(3.5) እንዲሁም አንቀጽ 29(1) መሰረት ላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን የመምረጥና የመሾም ሥልጣን የባለአክሲዮኖች መሆኑንና ይህም በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ወቅት ተግባራዊ እንደሚደረግ አስቀምጧል፡፡

የአንድ አክስዮን ማህበር መልካም አስተዳደር ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የዳይሬክተሮችን ቦርድ አባላት ምርጫ ሂደት ግልፅነት የተላበሰ እንዲሆን ማስቻል ሲሆን ይህንን እውን ለማድረግ ያግዝ ዘንድ የብርሃን ባንክ አ.ማ. ባለአክስዮኖች 10ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ “የብርሃን ባንክ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 2/2012”፤ ታህሣሥ 2 ቀን 2012 ዓ.ም. በማጽደቅ በመመሪያው መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ መመሪያ ወጥቶ የነበረው በወቅቱ በሥራ ላይ በነበረው በ1952 ዓ.ም. በወጣው የንግድ ሕግ፤ በ2000 ዓ.ም በወጣው የባንክ ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 592/2000 እና በዚሁ አዋጅ ማሻሻያ ቁጥር 1159/2011 እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ2019 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው የባንክ መልካም አስተዳደር/Bank Corporate Governance/ መመሪያ ቁጥር SBB/71/2019 መሰረት ነበር፡፡ ይሁንና የባንክ መልካም አስተዳደር “Bank Corporate Governance Directive No. SBB/71/2019፣ በSBB/91/2024”. የተተካ በመሆኑ፤ እንዲሁም በ1952 ዓ.ም. ወጥቶ የነበረው የንግድ ሕግ በ2013 ዓ.ም. በወጣው

የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1143/2013 የተተካ በመሆኑ; እንዲሁም ቀደም ሲል ወጥቶ የነበረው የባንክ ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 592/2008 እና በ1159/2011(እንደተሻሻለ) በባንክ ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 1360/2017 የተተኩና የተሻሩ በመሆናቸው ፤ እነኚህንና ሌሎች ተያያዥ ያላቸውን አዋጆችና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ ከጊዜው ጋር አብሮ የሚሔድ ፖሊስና የአፈጻጸም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው የባንክ መልካም አስተዳደር"Bank Corporate Governance Directive No. SBB/91/ 2024". አንቀጽ 9.1 ዳይሬክተሮች መጠቆምና መመረጥ ያለባቸው አስቀድሞ በጠቅላላ ጉባኤ በጸደቀ የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ መሰረት መሆን እንዳለበት፤ ይህም ፖሊሲና መመሪያ በባንክ መልካም አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/91/ 2024 የተደነገጉትንና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ማካተት እንዳለበት ያስገንዝባል።

ስለሆነም ባንካችን አግባብነት ያላቸውን የባንክ መልካም አስተዳደር "Bank Corporate Governance Directive No. SBB/91/ 2024" ድንጋጌዎች ያካተተ፤ በባንካችን/በማህበራችን/ ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፤ የባንኩን ጥቅሞች ከሁሉ በተሻለ ለማስጠበቅ፤ የባንኩን ሥራ አመራር የሚመሩ እና የሚቆጣጠሩ፣ ለዚህም ሐቀኛ፣ የመሪነት ክህሎት እና ብቃት ያላቸውን እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ለማቅረብ እንዲረዳ በማሰብ ይህንን የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ አዘጋጅቷል።

ስለሆነም የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በምን መልኩ እንደሚከናወን፤ ሊያሟሉት ስለሚገባው መስፈርት እንዲሁም ዳይሬክተሮች ሊኖራቸው ስለሚገባው ስብጥር የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ መቼ እና እንዴት እንሚመረጡ፤ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ያካተተና በዳይሬክተሮች

ምርጫ ወቅት ጠቅላላ ጉባኤው ሊከተለው የሚገባውን ሥርዓት ለመደንገግ የብርሃን ባንክ አ.ማ. 16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይህን የዳይሬክተሮች የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1 ርዕስ**

1. ይህ ፖሊሲና መመሪያ "የብርሃን ባንክ አ.ማ. ዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ ቁጥር 3/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ በሌላ አኳኋን ካልተተረጐመ በስተቀር፣ በዚህ ፖሊሲና መመሪያ ውስጥ ያሉት ቃላት ከዚህ በታች የተሰጣቸውን ትርጓሜዎች ይይዛሉ፡-

**2.1 "ባንክ" ማለት ብርሃን ባንክ አ.ማ. ማለት ነው፡፡**

**2.2 "ቦርድ"** ማለት በባለአክሲዮኖች የሚሾም የባንኩ የበላይ አካል ሲሆን ለባንኩ አስተዳደርና አፈጻጸም ቀዳሚ ተጠያቂነት ያለው፣ የባለአክሲዮኖችን እና የባለድርሻ አካላትን ጥቅም የሚያስጠብቅና አጠቃላይ ባንኩን በበላይ ሃላፊነት የሚቆጣጠር የብርሃን ባንክ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው።

**2.3 "ዋና ስራ አስፈጻሚ"** ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራዎችን በዋና ኃላፊነት የመምራት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው።

**2.4 "ዳይሬክተር"** ማለት በማንኛውም የማዕረግ ስም የሚጠራ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው።

2.5 “**ሠራተኛ**” ማለት የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራዎችን እንዲያከናውን በባንኩ የተሾመ ወይም የተቀጠረ ወይም በሠራተኛ ዝውውር አማካኝነት የተመደበ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው ነው፡፡

2.6 “**የመጀመሪያ ደረጃ የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና**” ማለት የትዳር አጋር፣ ልጆች እና ወላጆች ማለት ነው፡፡

2.7 “**አስፈጻሚ ያልሆነ ዳይሬክተር**” ማለት በባንኩ የቀን ተቀን አስተዳደር ውስጥ ተሳትፎ የሌለው እንዲሁም በባንኩ እና ተቀጽላዎቹ የሙሉ ጊዜ ሰራተኛ ያልሆነ ግለሰብ ማለት ነው።

2.8“**ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን ወይም ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ** ” ማለት ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ በአንድ ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተያዘ ሁለት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የአክስዮን ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን ማለት ነው።

2.9“**ተጽዕኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክሲዮን**” ማለት ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከሁለት በመቶ በታች የሆነ የአክሲዮን ድርሻ ባለቤት የሆነ ባለአክሲዮን ነው።

2.10 “**ሰው**” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

2.11 "**ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው ሰው**" ማለት ተጽእኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮኖች፣ ዳይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና የባንኩ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች ናቸው።

2.12 “**ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ**” ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሥራ ክፍሎችን የሚመራ እና ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም በቀጥታ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የሚያቀርብ እና ለዋና ሥራ አስፈጻሚ በምክትል ደረጃ ያሉ የሥራ መሪዎችን የሚያጠቃልል ማንኛውም የባንኩ ኦፊሰር ነው።

**2.13 "ጊዜያዊ ኮሚቴ" ወይም "ኮሚቴው ወይም** "አስመራጭ ኮሚቴ" ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀፅ 9.2 መሠረት እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሠረት የሚመረጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና ምርጫ አስፈፃሚ ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው፡፡

**2.14** "ጠቅላላ ጉባዔ" ማለት የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማለት ነው፡፡

**2.15 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጡ መመሪያዎች ወይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረጎች እንደአስፈላጊነቱ** ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ 3 ስለጾታዊ አገላለጽ፤**

በተለየ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር በወንድ ጾታ የተገለጸው ሁሉ ለሴትም የሚያገለግል ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈፃፀም ፖሊሲ

**አንቀጽ 4 . የቦርድ አባላት ምርጫ ፖሊሲ መርሆዎች፤**

የባንኩ የምርጫ ፖሊሲ መርሆዎች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

4.1 ብቃት ያላቸው፤ሀቀኛ፣ ጠንቃቃ፣ መልካም ስም ና እና ሥነ ምግባር ያላቸው ዳይሬክተሮች እንዲመረጡ ማድረግ፤

4.2 አስፈላጊው የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ እስካላቸው ድረስ የባለአክስዮኖችን የመምረጥና የመመረጥ መብትን ባከበረ መልኩ ግልጽና ፍትሀዊ የዕጩዎች ጥቆማና

የዳይሬክተሮች ምርጫ ማከናወን ፤

4.3 የዳይሬክተሮች ምርጫ ሲከናወን የባንኩን የሥራ ውጤታማነት ለማረጋገጥ፤ የታዩ መልካም ውጤቶችን ለማስቀጠልና፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚታዩ ችግሮች ካሉ ለማረም የሚያስችል በቂ የሆነ የሙያ ስብጥር፣ የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያላቸው እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ ማ ከ ና ው ን ፤

4.4 ችሎታ ያላቸውና ታማኝ የሆኑ የባንኩን ፋይናንስ አስተዳደር ማሳደግ የሚችሉና እሴት የሚጨምሩ የቦርድ አባላት እንዲመረጡ ማድረግ፤

4.5 ምርጫው የሙያ ስብጥር እንዲኖር በሚያረጋግጥና የተለያዩ ሙያዎች፣ ክህሎቶችና ልምዶች ባለቤት የሆኑና ሁለንተናዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል በባንክና ቢዝነስ ሥራዎች ላይ አስፈላጊው ክህሎት፣ እውቀትና ልምድ ያላቸው የቦርድ አባላት እንዲኖሩት ማስቻል፤

4.6 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በጾታ፤ በትምህርት ዝግጅት፤ በባለአክስዮኖችና ገለልተኛ የቦርድ አባላትን ስብጥር በያዘ መልኩ እንዲከናወን ማድረግ፤

4.7 በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን አክብረው የሚያስከብሩና በሕጉ መሰረት የባንኩን ባለአክስዮኖችንና የባለድርሻ አካላትን መብትና ጥቅም ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ለማስጠበቅ የሚችሉ የቦርድ አባላት እንዲመረጡ ማድረግን ያካትታል፡፡

**አንቀጽ 5 የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው ስልጣንና ሃላፊነት**

አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና በባንኩ የመመሥረቻ ጽሑፍ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ጉባዔው ከዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

5.1 ይህንን የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ ፖሊሲ እና የአፈፃጸም መመሪያ የማፅደቅ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማሻሻል፤

5.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን የመምረጥ፤

5.3 የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና ምርጫ ጊዜያዊ ኮሚቴን የመምረጥ/የመሰየም።

**አንቀጽ 6 የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና ምርጫ ጊዜያዊ ኮሚቴ አባላት**

6.1 የጊዜያዊ ኮሚቴው አባላት በባንኩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ይሆናል፡፡

6.2 ኮሚቴው አምስት (5) አባላት ይኖሩታል፡፡

6.3 በስራ ላይ ያሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እንዲሁም የባንኩ ሰራተኞች የአስመራጩ ኮሚቴው አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም፡፡

6.4 የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ሆነው ከሚመረጡ አባላት መካከል ቢያንስ ሁለቱ ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች መሆን አለባቸው፡፡

6.5 አስመራጭ ኮሚቴው በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 12 እና 13 መሰረት የሚመረጥ ይሆናል።

**አንቀጽ 7 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ብዛትና ስብጥር**

7.1 ባንኩ አስራ አንድ (11) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይኖሩታል።

7.2 ከሚመረጡት ጠቅላላ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ውስጥ፡-

7.2.1 1/3ኛው የቦርድ አባላት የሚመረጡት ተፅዕኖ ፈጣሪ ካልሆኑ ባለአክሲዮኖች መሆን አለበት።

7.2.2 1/3ኛው የቦርድ አባላት የሚመረጡት ከሁሉም ባለአክሲዮኖች መሆን አለበት።

7.2.3 1/3ኛው ገለልተኛ የቦርድ አባላት መሆን ያለበት ሲሆን የሚመረጡትም በሁሉም ባለአክሲዮኖች ይሆናል።

7.3 ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ውስጥ ቢያንስ ሁለቱ ዳይሬክተሮች ሴቶች መሆን አለባቸው፡፡

7.4 ከሁለት ያልበለጡ የባንኩ ሠራተኞች በቦርድ አባልነት ሊመረጡ ይችላሉ።

7.5 የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ሰዎች ገለልተኛ የቦርድ አባል ሆነው መመረጥ ይችላሉ።

7.6 የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት በተቻለ መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15.1.16 እና አንቀጽ 15 ላይ ከተጠቀሱት የተለያዩ የሙያ ዘርፎች የተውጣጡ መሆን ይገባቸዋል።

**አንቀጽ 8 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ**

8.1 የጥቆማ እና ምርጫ ጊዜያዊ ኮሚቴ የእጩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ የሚቀበለው የቦርድ ምርጫ የሚያከናውነው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በሚደረግበት ቀን ይሆናል።

8.2 በስራ ላይ ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ የእጩ ገለልተኛ ቦርድ ዳይሬክተሮች አባላትን ዝርዝር ለጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው ያቀርባል። ቦርዱ የእጩ ገለልተኛ ቦርድ አባላት ምልመላ የሚያደርገው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ እና በዚህ ፖሊሲ እና መመሪያ አንቀጽ 18 መሠረት ይሆናል።

8.3 ጊዜያዊ ኮሚቴው የሚያስመርጣቸው ሁሉም እጩዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተገለጹትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት።

8.4 ጊዜያዊ ኮሚቴው የእጩነት ጥቆማ አሰጣጡም ግልጽነት ያለው እና ይህንን የአሰራር መመሪያ ተከትሎ የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

8.5 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ላይ በተጠቀሰው መሰረት ይከናወናል።

**አንቀጽ 9 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ማሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች**

9.1 ለቦርድ አባልነት የሚመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና በንግድ ሕግ የተደነገጉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

9.2 ባንኩ ጠቅላላ ጉባዔ ከመካሄዱ አስቀድሞ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ማሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች እና ስለሚመረጡበት ፕሮሲጀር (ሂደት) ባለአክሲዮኖቹ እንዲያውቁት ማድረግ አለበት።

9.3 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 እና 15 የተዘረዘሩት ናቸው።

**አንቀጽ 10 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ**

10.1 ማንኛውም ሰው የዳይሬክተሮች ቦርድ ኣባል ለመሆን በቅድሚያ እጩ ዳይሬክተር ሆኖ መጠቆም አለበት፡፡

10.2 ከእጩ ገለልተኛ ዳይሬክተሮች በስተቀር የሌሎች ዳይሬክተሮች ጥቆማ የሚደረገው የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በሚያከናውነው የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በሚካሔድበት ቀን ነው፡፡

10.3 የዳይሬክተሮች ቦርድ የእጩ ገለልተኛ ዳይሬክተሮች ስም ዝርዝርና ደጋፊ ማስረጃዎች ለአስመራጭ ኮሚቴው በጉባኤው እለት ከምርጫው አስቀድሞ ማስረከብ አለበት፡፡

10.4 በዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ከፍተኛ ድምፅ ያገኙ እጩዎች በቦርድ አባልነት ይመረጣሉ።

10.5 በምርጫው በቦርድ አባልነት ያልተመረጡት ባገኙት ድምፅ መሠረት በተጠባባቂነት ይያዛሉ።

10.6 የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ የሚካሄድበት ዝርዝር ሂደት በዚህ መመሪያ በክፍል ሶስት በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

10.7 ኮሚቴው የቦርድ አባላት ምርጫው ግልጽነት ያለው እና ይህንን የአሰራር መመሪያ ተከትሎ የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

# ክፍል ሦስት

# የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ

**አንቀጽ 11 የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና ምርጫ ጊዜያዊ ኮሚቴ አባላት አመራረጥ**

11.1 የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በሚከናወንበት ቀን የጊዜያዊ ኮሚቴው አባላት ምርጫን ማከናወን የመደበኛ ጉባዔው የመጀመሪያ አጀንዳ ይሆናል። የዳይሬክተሮች ቦርድም ይህንን የጉባዔውን የመጀመሪያ አጀንዳ አድርጎ የማቅረብ ሃላፊነት አለበት።

11.2 የጊዜያዊ ኮሚቴው አባላት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ በሚከናወንበት ቀን በባንኩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከባለአክሲኖች ይመረጣሉ።

11.3 የጊዜያዊ ኮሚቴ አባላትን የሚያስመርጠው ቦርዱ ነው።

11.4 የጊዜያዊ ኮሚቴው አባላት ከጉባዔው አባላት በሚቀርብ ጥቆማ መሰረት ይመረጣሉ።

11.5 በጥቆማውም የኮሚቴው አባል ሆነው ለማገልገል ፈቃደኛ የሆኑ አስር እጩዎች ተጠቁመው ከዚያ ውስጥ በሚያገኙት ከፍተኛ ድምፅ አምስቱ በኮሚቴ አባልነት ይመረጣሉ።

**አንቀጽ 12 የጊዜያዊ ኮሚቴው አባላት የሚመረጡበት መስፈርት**

ጊዜያዊ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ሆነው የሚመረጡት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ) የባንኩ ባለአክሲዮን የሆኑ፤

ለ) በአስመራጭነት ለመሥራት ፍላጐት ያላቸው፤

ሐ) የባንኩ ቦርድ አባል ወይም ተቀጣሪ ሠራተኛ ያልሆኑ፤

**አንቀጽ 13 የጊዜያዊ ኮሚቴው ኃላፊነቶች**

13.1 የኮሚቴው አባላት በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው እንደተመረጡ በመሰብሰብ ከመካከላቸው ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይመርጣሉ።

13.2 ኮሚቴው በባንኩ የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 29 (1) መሠረት አስራ አንድ (11) አባላት ያሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው ያስመርጣል።

13.3 ኮሚቴው ቀጥሎ በተገለፀው አኳኋን እጩዎችን በሶስት ምድብ መቀበል እንዲቻል ሶስት የእጩ ጥቆማ መቀበያ ሰነድ ያዘጋጃሉ። እነርሱም፡-

13.3.1 ምድብ አንድ፡- ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ ጥቆማ የሚያቀርቡበትና የሚመርጡበት የ1/3ኛ የቦርድ አባላት የጥቆማ መቀበያ ሰነድ፤ (በዚህ ምድብ የሚመረጡት ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ ናቸው) ፤

13.3.2 ምድብ ሁለት፡- ሁሉም ባለአክሲዮኖች ጥቆማ የሚያቀርቡበትና የሚመርጡበት የ1/3ኛ የቦርድ አባላት የጥቆማ መቀበያ፤ (በዚህ ምድብ ሁሉም ባለአክሲዮኖች በጥቆማ እና በምርጫ ይሳተፋሉ) ። እንዲሁም፤

13.3.3 ምድብ ሶስት፡- ሁሉም ባለአክሲዮኖች በመምረጥ የሚሳተፉበት የ1/3ኛ ገለልተኛ የቦርድ አባላት የእጩዎች ዝርዝር መቀበያ ሰነድ ናቸው።

13.4 በአንቀጽ 13.3. መሠረት የሚዘጋጀው የጥቆማ ሰነድ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ ይሆናል፤

13.4.1 የተጠቋሚውን ሙሉ ስም፣

13.4.2 ዕድሜ፣

13.4.3 የትምህርት ደረጃ፣

13.4.4 የትምህርት ዘርፍ፣

13.4.5 የስራ ልምድ።

13.5 ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው የእጩዎች ጥቆማ እንዲሁም የድምጽ አሰጣጥን በተመለከተ ተገቢውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለፃ ይሰጣሉ ወይም እንዲሰጥ ያደርጋሉ።

13.6 በአንቀፅ 13.3 ስር በተገለፀው ምድብ አኳኋን የእጩዎችን ጥቆማ ይቀበላሉ።

13.7 በአንቀጽ 13.3. ስር በተገለፀው ምድብ አኳኋን ባለአክሲዮኖች ለእጩዎቹ ድምጽ እንዲሰጡ ያደርጋሉ፤ እንዲሁም ሙሉ የምርጫ ሂደቱን ይመራሉ።

13.8 ሁሉም እጩዎች በዚህ መመሪያ የተገለፁትን (በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና በንግድ ሕግ የተገለፁትን) መስፈርቶች ማሟላታቸውን ያረጋግጣል።

13.9 የምርጫ ውጤቱን ለባለአክሲዮኖች ይገልፃል፤ እንዲሁም በውጤቱ ላይ በመፈራረም የጉባዔው ቃለ ጉባኤ አካል ሆኖ እንዲመዘገብ ለቦርዱ ያስረክባል።

**አንቀጽ 14 ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች**

14.1 በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚመረጡት የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡-

14.1.1 ባንኩን በቦርድ አባልነት ለማገልገል ፈቃደኛ የሆኑ፤

14.1.2 መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው፤

14.1.3 ታማኝ፣ ሀቀኛ፣ እና መልካም ዝና ያላቸው፤

14.1.4 የህዝብ ጥቅም ለመጠበቅ የወጣ ሕግ በመተላለፍ በማጭበርበር፣ እምነት በማጉደል፣ ተከሰው በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሠጥቶባቸው የማያውቅ፤

14.1.5 በራሳቸው ወይም እነሱ በዋና ባለቤትነት በያዟቸው ድርጅትን በሚመለከት ለሕዝብ መገለጽ ያለበትን መረጃ ደብቀው የማያውቁ፣ ሃሰተኛ የሂሳብ መግለጫ አቅርበው የማያውቁ፣ የተቆጣጣሪ አካላትን ውሳኔ ላለመቀበል ወይም ላለመገዛት እምቢተኛ ሆነው የማያውቁ፣

14.1.6 በዋና ባለቤትነት የያዙት ድርጅት ተመርምሮ እምነት በማጉደል፣ በማጭበርበር ወይም በተመሳሳይ ጥፋት በተቆጣጣሪ አካል፣ በፍ/ቤት ወይም ትራይቡናል የዲሲፕሊን እርምጃ፣ ዕገዳ ወይም ቅጣት ተላልፎባቸው የማያውቅ፤

14.1.7 በራሳቸው ወይም ዳይሬክተር ወይም ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም ስራ አስፈጻሚ በሆኑበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት ወይም የኪሳራ ውሳኔ ያልተሰጠበት፣ በኪሳራ ምክንያት ንብረታቸው ለዕዳ ማቻቻያ ያልተወሰደባቸው፣

14.1.8 በራሳቸው ወይም ዳይሬክተር ወይም ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም ስራ አስፈጻሚ የሆኑበት ድርጅት የባንክ ወይም ሌላ ብድር ወይም ታክስ ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረታቸው በሃራጅ ያልተሸጠባቸው፣

14.1.9 በራሳቸው ወይም ዳይሬክተር ወይም ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም ስራ አስፈጻሚ የሆኑበት ወይም ባለቤት የሆኑበት ድርጅት የተበደረውን ገንዘብ ባለመክፈሉ ብድሩ ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ ጤናማ ያልሆነ ምድብ ውስጥ ገብቶ የማያውቅ፤

14.1.10 ባለአክስዮኑ አክሲዮን የገዙበትን ገንዘብ ያገኙት ከከሰረ ሰው ወይም በአስተዳደር ችግር ምክንያት ኪሳራ ካጋጠመው ሰው ያልሆነ ወይም ገንዘቡን ያገኙት በማጭበርበር ወይም በህገ-ወጥ መንገድ ያልሆነ፤

14.1.11 ባለአክስዮኑ የአክስዮኑ ባለቤት በሆኑ ጊዜ የነበራቸው የሀብት መጠን ከአክሲዮኖቹ ዋጋ በላይ የነበረ፤

14.1.12 በቂ ስንቅ/ገንዘብ ሳይኖራቸው ቼክ ሰጥተው ሂሳቡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ያልተዘጋባቸው፤።

14.1.13 በአንቀጽ 14.1. ላይ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በምድብ አንድ እና በምድብ ሁለት የሚመረጡ የቦርድ አባላት የሚከተሉትን መስፈርቶች በተጨማሪነት ማሟላት አለባቸው፡-

14.1.14 የቦርድ አባላት ምርጫ የሚያከናውነው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከመካሄዱ አስቀድሞ ቢያንስ ለሁለት ዓመት ባለአክሲዮን የነበሩ፤

14.1.15 ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያላቸው፤

14.1.16 በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በባንኪንግ እና/ወይም ፋይናንስ፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በሕግ፣ ሪስክ ማኔጅመነት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በመሳሰሉት የትምህርት ዘርፎች ቢያንስ ሰባት (7) ዓመት የስራ ልምድ ያላቸው፤

14.1.17 በሌሎች ከአራት በበለጡ ተቋማት ውስጥ የቦርድ አባል በመሆን በማገልገል ላይ የማይገኙ፤

14.1.18 ከዚህ በፊት በንግድ ማኅበር አደራጅነት፣ ዳይሬክተርነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ ኦዲተርነት ወይም በሌሎች የአመራር ኃላፊነቶች ላይ ተመድበው ሲሰሩ ከኃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ በእምነት ማጉደል፣ በስርቆት ወይም በውንብድና ወይም ለቦርድ አባልነት ብቁ በማያደርግ ተመሳሳይ ወንጀል ጥፋተኛነታቸው ያልተረጋገጠ፤

14.1.19 የሌላ ባንከ ሠራተኛ ያልሆኑ፤

14.1.20 የሌላ ፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ያልሆኑ፤

14.2 ከላይ በአንቀጽ 14.1 እና 14.2 ላይ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚ በሌላ ድርጅት ውስጥ አስር በመቶ (10%) እና ከዚያ በላይ

አክሲዮን ካለው ድርጅቱ (የዳይሬክተሮች ቦርድ አባሉ ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚው ባለአክሲዮን የሆነበት ድርጅት) የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ መመረጥ አይችልም።

14.3 ለቦርድ አባልነት በእጩነት የሚጠቆመው የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሆነ ድርጅቱን በመወከል በቦርድ አባልነት የሚያገለግለው ሰው በአንቀጽ 14.1 እና 14.2 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ድርጅቱን የሚወክል ሰው ማንነት አብሮ መገለጽ አለበት።

14.4 ከሚመረጡት ጠቅላላ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ውስጥ ቢያንስ ሁለቱ ሴቶች መሆን አለባቸው።

14.5 ማንኛውም ዳይሬክተር በራሱም ሆነ በውክልና ከስድስት ተከታታይ አመታት በላይ በቦርድ አባልነት መመረጥ አይችልም። ሆኖም ጠቅላላ ጉባኤው የስራው ቀጣይነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነበት ከጠቅላላው የቦርድ አባላት ቁጥር ከአንድ ሶስተኛ ያልበለጡትን ለሶስተኛ ዙር በቦርድ አባልነት እንዲሰሩ ሊመርጣቸው ይችላል።

**አንቀጽ 15 ገለልተኛ ዳይሬክተሮች ሊያሟሉት የሚገባው መስፈርት**

15.1 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ላይ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በምድብ ሶስት የሚመረጡ ገለልተኛ የቦርድ አባላት የሚከተሉትን መስፈርቶች በተጨማሪነት ማሟላት አለባቸው፡-

15.1.1 ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም ቢያንስ ሁለተኛ ዲግሪ በባንኪንግ፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በኦዲት፣ በፋይናንስ፣ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣ በቴክኖሎጂ፣ እና በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ያላቸው፤

15.1.2 በፋይናንስ ሴክተር ውስጥ በመስራት ወይም የፋይናንስ ወይም ኦዲትንግ ወይም ሪስክ ማኔጅመንት ወይም ተመሳሳይ ዘርፍ በማስተማር ወይም በአማካሪነት ቢያንስ 10 አመት የስራ ልምድ ያላቸው፤

15.2 የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ሰዎች የገለልተኛ ቦርድ አባል ሆነው መመረጥ ይችላሉ።

**አንቀጽ 16 የምርጫ መስፈርቶችንና ፕሮሲጀር (ሂደት) ለባለአክሲዮኖች ስለማሳወቅ**

የማህበሩ ጸሐፊ መደበኛው ጠቅላላ ጉባኤ ከመደረጉ አንድ ወር በፊት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚመረጡበት መስፈርቶች የሚገልጽ መግለጫ ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች፣ በባንኩ በይነ መረብ (ድረ-ገጽ) ፣ እንደአስፈላጊነቱ በብሮድካስት እንዲሁም በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ለባለአክሲዮኖች እንዲገለጽ ያደርጋል።

**አንቀጽ 17 እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማ ሂደት**

## 17.1 ጠቅላላ ድንጋጌ፡-

17.1.1 ባንኩ ጠቅላላ ጉባዔ ከመካሄዱ አስቀድሞ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስለሚመረጡበት ሂደትና ሊያሟሉት ስለሚገባው መስፈርት ባለአክሲዮኖቹ እንዲያውቁት ያደርጋል።

17.1.2 የጥቆማ እና ምርጫ ጊዜያዊ ኮሚቴ የእጩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ የሚቀበለው የቦርድ ምርጫ የሚያከናውነው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በሚደረግበት ቀን ነው።

**17.2 የጥቆማ አቀባበል፡**

**17.2.1 በምድብ አንድ እና ሁለት ለሚመረጡ የቦርድ አባላት፡-**

**17.2.1.1** በእያንዳንዱ ምድብ ለሚደረገው ምርጫ የሚመረጡትን የቦርድ አባል እጥፍ እጩዎችን ጥቆማ ይቀበላል።

**17.2.1.2** የእጩነት ጥቆማዎቹ በግልጽ የእጩውን የትምህርት ደረጃ፣ የስራ ልምድ እንዲሁም ጥቆማውን የሚሰጠውን ባለአክስዮን ማንነት የሚገልፅ መሆኑን ኮሚቴው ያረጋግጣል። ጠቋሚዎቹ በጥቆማ ጊዜ ይህንን ሙሉ መረጃ መስጠት ካልቻሉ ተጠቀሚዎቹ ወዲያውኑ ተጠይቀው መረጃውን እንዲሰጡ ይደረጋል።

**17.2.1.3** የሚጠቆመው እጩ የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሆነ ድርጅቱን በመወከል በቦርድ አባልነት የሚያገለግለው ሰው ማንነት፣ የትምህርት ደረጃ፣ እና ስራ ልምድ አብሮ እንዲገለፅ ኮሚቴው ያደርጋል። በዕለቱ ይህንን ማረጋገጥ ካልተቻለ ድርጅቱ በቀጣይ እንዲያሟላ ይደረጋል።

**17.2.1.4** የሚጠቆሙት እጩዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ኮሚቴው ተጠቋሚዎቹን በመጠየቅ ያረጋግጣል።

**17.2.2 በምድብ ሶስት ለሚመረጡ ገለልተኛ የቦርድ አባላት ፡-**

17.2.2.1 በእጩነት የሚቀርቡት የገለልተኛ ቦርድ አባላት ከቦርዱ አባላት ውስጥ 1/3ኛ ሲሆኑ ለዚህም ከሚመረጡት ዳይሬክተሮች እጥፍ የሆኑ እጩዎች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

17.2.2.2 እጩ ገለልተኛ የቦርድ አባላት በዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና ሪሙኔሬሽን ንዑስ ኮሚቴ ተመልምለው በቦርዱ በኩል ለኮሚቴው ይቀርባሉ።

17.2.2.3 በእጩነት የሚቀርቡት የገለልተኛ ቦርድ አባላት በአንቀፅ 14 እና 15 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው።

17.2.2.4 በተለይም ገለልተኛ የቦርድ አባል ለመሆን በእጩነት የሚቀረቡ ሰዎች የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆናቸውን ቦርዱ ማረጋገጥ አለበት ፡-

ሀ. ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ባለአክሲዮን ያልሆኑ፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ስራ አስፈጻሚ ወይም የባንኩ ሠራተኛ ያልሆኑ ወይም ከእነዚህ ጋር የመጀመሪያ ደረጃ የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና የሌላቸው መሆኑን የማረጋገጥ፤

ለ. ከባንኩ ጋር ማንኛውም አይነት የውል ግዴታ ባለው ድርጅት ውስጥ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈጻሚ ያልሆኑ መሆናቸውን፤

ሐ. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በፍርድ ቤትም ሆነ ከፍርድ ቤት ውጪ ባሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ማንኛውንም አይነት የህግ ክርክሮች በባንኩ፣ በባንኩ እናት ድርጅቱ ወይም በባንኩ ተቀጽላዎች ላይ ያላቀረቡ መሆናቸውን እንዲሁም በባንኩ፣ በባንኩ እናት ድርጅት ወይም በባንኩ ተቀፅላ ላይ በተነሱ የህግ ክርክሮች ወይም ከፍርድ ቤት ውጭ ባሉ ክርክሮች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳታፊ ያልሆኑ/መሆን የሌለባቸው፣

መ. ባለፉት ሁለት ዓመት ውስጥ ከባንኩ ጋር ማንኛውንም የቢዝነስ፣ የንግድ እና ሙያዊ ግንኙነቶችን ያላደረጉ መሆናቸውን፣ እንዲሁም

ሠ. ከብር 50 ሚሊዮን በላይ የሆነ ማንኛውንም አይነት ገንዘብ ነክ የሆነ ሀላፊነት ከባንኩ ጋር ያላቋቋሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

17.3 በአጠቃላይ በሶስቱ ምድብ በእጩነት ከሚቀርቡ ተጠቋሚዎች ቢያንስ አራቱ ሴቶች መሆን አለባቸው።

17.4 ማንኛውም ባለአክሲዮን እራሱን በእጩነት ለማቅረብ ይችላል።

17.5 ኮሚቴው የእጩነት ጥቆማ አሰጣጡም ሆነ የቦርድ አባልነት ምርጫው ግልጽነት ያለው እና ይህንን የአሰራር መመሪያ ተከትሎ የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

**አንቀጽ 18 የድምፅ አሰጣጥ ሂደት**

18.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ ለምርጫው የሚያስፈልጉ ኮምፒዩተሮች፣ የድምጽ መስጫ ሳጥኖችና ሌሎች ቁሳቁሶች አስቀድመው እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡

18.2 ኮሚቴው እጩ ተጠቋሚዎች ራሳቸውን ለጠቅላላ ጉባዔው እንዲያስተዋውቁ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ለመሥራት ያላቸውን ፍላጐት እንዲገልጹ እድል መስጠት አለበት።

18.3 ባለአክሲዮኖቹ ለድምፅ መስጫ የተዘጋጀውን ካርድ በመጠቀም በእያንዳንዱ ምድብ ስር ለተጠቆሙት እጩዎች በተናጠል ድምጽ ይሰጣሉ፡፡

18.4 የድምጽ መስጫ ካርዱ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

ሀ. የባለአክሲዮኑን ስም፤

ለ. የባለአክስዮኑን የተፈረመ የአክስዮን ድርሻ (ድምፅ)፤

ሐ. የባንኩን ስም እና አርማ፤ እና

መ. ባለአክስዮኑ ሊመርጧቸው የሚፈልጉትን የእጩ ተጠቋሚ/ዎች ስም የሚፃፍበት ቦታ ;

18.5 የባለአክሲዮኖች በስብሰባ ላይ የመገኘት ፊርማ /አቴንዳንስ/ በሚወሰዱበት/በሚፈረምበት ጊዜ የድምጽ መስጫ ካርዶቹ ለባለአክሲዮኖቹ ይሰጣሉ።

18.5 በምድብ አንድ ስር ለቀረቡ እጩዎች ድምጽ መስጠት የሚችሉት ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ ናቸው።

18.6 በምድብ ሁለት እና ሶስት ስር ለቀረቡ እጩዎች ሁሉም ባለአክሲዮኖች ድምጽ መስጠት ይችላሉ።

18.7 ሆኖም ባንኩ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ባለአክስዮኖች የሌሉት ከሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በሁሉም ባለአክስዮኖች ይከናወናል።

18.8 ባለአክሲዮኖች በድምጽ መስጫ ካርዱ ላይ የሚመርጡትን እጩ/እጩዎች ስም ለዚሁ ተግባር በተሰጠው ቦታ ከጻፉና ከፈረሙበት በኋላ የድምፅ መስጫ ካርዱን ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ያስገባሉ።

18.9 የድምጽ መስጫ ካርዱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግድፈቶች ከተገኙበት ውድቅ ይደረጋል፤

ሀ. የባለአክስዮኑ ስም የሌለው ከሆነ፤

ለ. የባለአክሲዮኑን የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት(ድምፅ) የማያመለክት ከሆነ፤

ሐ. የባንኩ ስም እና አርማ ያልታተመበት ከሆነ፤ እንዲሁም

መ. የዕጩ ተመራጩ ስም ወይም ለምርጫው ተብሎ ለእጩው የተሰጠ መለያ ቁጥር ያልተጻፈበት ከሆነ፤ እንዲሁም

ሠ. የመራጩ ፊርማ የሌለበት ከሆነ፤

18.10 የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ በምርጫ ካርድ የተከናወነ እንደሆነ ኮሚቴው የድምጽ ቆጠራውን ለዘሁ ተግባር ሲባል ለማገዝ ከተመደቡት የባንኩ ሰራተኞች ጋር በመሆን ያከናውናል።

18.11 ኮሚቴው የድምፅ ቆጠራው ከተከናወነና ውጤቱ ለባለአክስዮኖች ከተገለጸ በኋላ የምርጫ ካርዶቹን ለማህበሩ ፀሓፊ ያስረክባል።

18.12 ኮሚቴው የድምጽ ቆጠራው እንደተጠናቀቀ የድምጽ አሰጣጡ እና የቆጠራ ሂደቱ እንዲሁም የምርጫው ውጤት ትክክለኛ ስለመሆኑ ለዚሁ በተዘጋጀ ፎርም ላይ በመፈራረም ማረጋገጥ አለበት፡፡

18.13 ኮሚቴው የድምጽ ቆጠራውን ውጤት ድምጽ በተሰጠበት ቀን ለጠቅላላ ጉባኤው ይገልጻል፡፡ ይህ የማይቻል ከሆነ ግን በቀጣዩ የሥራ ቀን በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ እንዲሁም በባንኩ ድረ-ገጽ ላይ በማውጣት እንድገለጽ ያደርጋል፡፡

18.14 በምርጫው በእያንዳንዱ ምድብ ከፍተኛ ድምጽ ያገኙ እጩዎች በቦርድ አባልነት ይመረጣሉ/ይሾማሉ፡፡ በምርጫው በተገኘው ድምፅ መሠረት እጩ ሆነው የተወዳደሩ ሴቶች በቦርድ አባልነት ለመመረጥ የሚያበቃ ድምጽ ያላገኙ እንደሆነ በአንቀጽ 18.15 ላይ የተደነገገው ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

18.15 በምርጫው የተወዳደሩ ሴት እጩዎች በቦርድ አባልነት ለመመረጥ የሚያስችል ድምፅ ያላገኙ እንደሆነ የሴቶችን የፆታ ተዋፅኦ ለመጠበቅ ሲባል በእጩነት ከቀረቡ ሴቶች መካከል ሁለቱ ባገኙት ድምፅ መሠረት በሽግሽግ በቦርድ አባልነት እንድሾሙ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን በየትኛውም ምድብ ውስጥ እጩ ሆነው ከቀረቡ ሴቶች መካከል አንዲት ሴት ባገኘችው ከፍተኛ ድምፅ መሠረት በቀጥታ በቦርድ አባልነት የተመረጠች እንደሆነ በሽግሽግ የመሾም መብቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ለአንዲት እጩ ሴት ብቻ ይሆናል፡፡

18.16 ያልተመረጡ እጩዎች ለወደፊት በቦርዱ ውስጥ ክፍት የስራ መደቦች ሲኖሩ በምርጫው ባገኙት ድምጽ መሠረት በቦርድ አባልነት ለመሾም በተጠባባቂነት ይያዛሉ፡፡

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 19 ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የማይሆንበት ሁኔታ**

19.1 ይህ መመሪያ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ተፈጻሚ አይሆንም።

19.1.1 የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አማካኝነት በሚካሄድበት ጊዜ፤

19.1.2 የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በፍርድ ቤት፣ በውጪ ኦዲተር ወይም ሌላ ስልጣን ባለው አካል እንዲደረግ የተወሰነ እንደሆነ ወይም የሚደረግ ከሆነ፤

19.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ከዚህ በላይ በተጠቀሱ አካላት በሚከናወንበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው ሕጎች እና መመሪያዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

**አንቀጽ 20 ድጋፍ ስለማግኘት**

የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና ምርጫ ጊዜያዊ ኮሚቴ ስራውን በአግባቡ መወጣት ያስችለው ዘንድ የእጩዎች ጥቆማ በሚደረግበት ጊዜ እንዲሁም በድምፅ አሰጣጥ እና በምርጫው ሂደት ላይ አስፈላጊው የሰው ሃይል እና የቁሳቁስ ድጋፍ እንዲደረግለት የባንኩን አመራር መጠየቅ ይችላል። የባንኩ አመራርም በኮሚቴው ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት።

**አንቀጽ 21 የሌሎች ሕጐች ተፈጻሚነት**

ለዚህ ፖሊሲ እና መመሪያ አፈጻጸም እንዲሁም በዚህ ፖሊሲ እና መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በሚመለከት ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሃገሪቱ ሕጐችና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 22 መሻሪያ**

በባንኩ የባለአክሲዮኖች 12ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ፀድቆ ሥራ ላይ የቆየው የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/2012 ተሠርዞ በዚህ መመሪያ ተተክቷል።

**አንቀጽ 23 ከዚህ ፖሊሲ እና መመሪያ ጋር ስለሚቃረኑ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች**

የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ እና ምርጫ በሚመለከት ከዚህ ፖሊሲና መመሪያ ጋር የሚቃረኑ የባንኩ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ካሉ ከዚህ ፖሊሲ እና መመሪያ አንፃር ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

**አንቀጽ 24 ማሻሻያ**

ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ በጠቅላላ ጉባዔው ሊሻሻል ይችላል።

**አንቀጽ 25 ተፈጻሚነት**

ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።